ዘዴኞች እንሁን

ትእይንት ፩

መጋረጃው ሲከፈት፡- ሁለት ታላቅና ታናሽ ወንድማማቾች ፣ አንድ እህት እንዲሁም አንድ እናት ሆነው ታላቅ ወንድማቸው እየሰከረና እየረበሸ ስላስቸገረ ተረባርበው በንግግር እየተጋገዙ የምክር ቃላቸውን ይለግሱታል። ይሔ ታላቅ ወንድማቸው ግን የማይሆን ምክንያት እየፈጠረ ሊያሳምናቸው ይሞክራል። በል ሲለው የጊዜ ማሳለፊያ አጣሁ ይላል። አንዳንዴ ደግሞ ጓደኞቼ አስቸግረውኝ ነው ይላል። ነገር ግን እነሱ ፍፁም አይሰሙትም። የሱ እያመሸ መግባትና የሱ ጩኸት ስለ ሰለቻቸው ሁሉም የስካርን ጉዳት እያነሱ ሲጨቀጭቁት ተመናጭቆ ይወጣል።

እነሱ ግን እርስ በርሳቸው እግዚአብሔር ልቦና ይስጠው ተባባሉ። እናታቸውም እንዲህ አሉ ልጆቼ እንግዲህ እግዚአብሔር ብሎልኝ እኔ የምወደው ሊቀ መለአክት ቅ/ገብርኤል ሰምቶኝ ስእለቴም እስኪሰምር ድረስ ከእናንተ አፍ ምንም ቢበድል ምን አደራችሁን ምንም ክፉ ነገር እንዳትናገሩት ልጆቼ።እንዲው ልጄ አንተ በተለይ አደራህን። ለልጅነቱ እናንተ ትበቁኛላችሁ።

ትንሹ ልጅ ደረጄ እንዲህ አለ። እማዬ ይሄ ጭንቅላት የሌለው ሆኖ ነው እንጂ እንዴት ጠዋት የወጣ ማታ ይመጣል? ከማታም በለሊት 6 ሰአት እኛስ ልጅ ነን ምንም አይደል። እናቴ ታስባለች ትደክማለች አይልም? መቼም እሱ ካልመጣ እሺ ብለሽ አትተኚም ይህን እያወቀ ... አያለ ሲነጫነጭ መጋረጃው ይዘጋል።

ትእይንት ፪

መጋረጃው ሲከፈት፡- ትንሿ ሴት ልጃቸው ሀና ቡና እያፈላች ነው። ሲኒ ደርድራ አቀማመጧን አሳምራ ቁጭ ብላለች። እናታቸው ደግሞ ጥጥ ይፈትላሉ ቆንጆ መቀመጫ ላይ ተቀምጠው። ትንሹ ልጅ ደረጄ ደግሞ ደብተሩን ገልጦ እየፃፈ ያጠናል።

እናታቸው የሚፈትሉትን ጥጥ ቆም አድርገው ወይ ይሄ ልጅ ዛሬማ ጭራሽ ባሰበት አይደል እንዴ።

ሐና ፡- እማዬ እኔ ልናገር ስል ቀደምሽኝ ከለሊቱ 7 ሰአት ሊሆን እኮነው። በዚህ ከቀጠለ ወንድም ጥላ ሄዶ ሄዶ ማንጋቱ አይቀርም።

ደረጄ፡- ጥናቱን ቆም አደረገና ቡናውን በስኒ እንደያዘ ቆይቆይ ሐና ቆይ እስቲ ብሎ ፀጥ ያደርጋቸዋል። የመጣ መስሎኝ ነው ይላል። ምንም ኮሽታ ሲያጡ ወደ ጫጫታቸው ይመለሳሉ።

በዚህ አጋጣሚ እየተወላገደና እየጮኸ የውጪውን በር አያንኳኳ ይጣራል። እነሱ ግን ጫጫታቸው፣ ድምፃቸው ከፍ ከማለቱ የተነሳ ጫጫታው ሞቅ አድርጎታል። መስማት አይቀርምና ሰሙ። ሐና ሮጣ ከፈተችለት እየተወላገደ እየተንተባተበ በመናገር ይገባል። እንዲህም ይላል።

ምንድነው ሰው ከጓደኞቹ ጋር ተጫውቶ ቁም ነገር ተነጋግሮ መግባት አይችልም አንዴ? ምንድነው በር ተዘግቶ የሚጠብቀኝ ብሎ ሌላም ሌላም እየተናገረ ይደነፋል።

እናታቸው ፡- ልጄ ትንሽ ገርበብ አድርጌ የዘጋሁት እኔ ነኝ ጭራሽ ባንተው ብሶ ትቆጣለህ እንዴ እንዴት ያለው ጉድ ነው። በል እስቲ በል እዚያችጋ አረፍ በልና እራት ልበለው እንጂ እራት በልተህ ትተኛለህ። ሲባል እሱ ግን የምን እራት ነው። አንተ ምን አባክ ነው እኔ ስመጣ ቁጭ ብለህ የምታየኝ ብሎ የደረጄን ደብተር ነጥቆ ይጨረማምተዋል ሲላፉ ሲታገሉ ለ3 ሆነው እንደ ምንም ደብተሩን ነጥቀው ያስቀምጣሉ።

ደረጄም፡- እየተነጫነጨና እየተቆጣ ወደውጭ ወጣ አለ።

እናታቸው ፡-ደግሞ ደረጄ ልጄ በማታ የት ነው የምትሄደው ና እንጂ ይላሉ።

ሐና፡- ወንድምዋላ አበዛሽው አሁንስ ስትል

እሱ ደግሞ፡- ዝም በይ ዝም በይ ህፃን ይላል እየተወላገደ ይቆጣል።

እናትየው፡- በልኮ በል ሂድ ተኛ ነው የምልህ። እኔን አታሰቃየኝ ምነው እቴ። በልሂድተኛ ብለው እንደ መቆጣት ይላሉ።

እሱም፡- የሰከርኩ መስሏችሁ በኔ ትጮሃላችሁ። ቆይ ቆይ እማዬ ቆይ እያለ ወደ መኝታ ክፍሉ ይገባል።

ሐና፡- የደረጄን ደብተር ሰብስብ አድርጋ ካስቀመጠች በኃላ ሲኒዋን ደርድራእያጣጠበች እንደ መበሳጨት ትላለች።

እናት፡- ወጣ ብለው ትንሹን ልጃቸውን ደረጄን ይዘውት የገባሉ። በህብረት ሆነው ቡናቸውን ከጠጡ በኃላ እነሱ እንደ በፊታቸው እየተጨዋወቱ እየተሳሳቁ እያለ መጋረጃው ይዘጋል።

ትእይንት ፫

መጋረጃው ሲከፈት ትልቁ ልጃቸው ወንድም ጣላ ተኝቷል። እናታቸውም በሌላ መንገድ ወደ ቤት ገባ ሲሉ ልጃቸው ተኝቶ ያገኙትና ይቀሰቅሱታል።

እናት፡- ተነስ እንጂ አንተ ተነስ። ወይ ጉድ የከብት መግቢያ ሰአት አይደለም እንዴ? ትናት ከልክ ያለፈ መጠጥ ጠጣህ ዛሬ ግን ቀኑን ሙሉ ስትተኛ ዋልክ እንደ በሽተኛ ይሉታል።

ወንድም ጥላ፡- አይ እማዬ ትላንት አይፈረድብኝም አንዱ ጓደኛዬ ውጪ ስለሚሄድ ለዚያ ነው እንደዚያ የሆንኩት።

እናት፡- አንተ መቼም ቢሆን ለምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ በተለይ! ለመጠጥ ለከት ቢኖርህ ይሻልሀል። ዋልህ።

ይሄ ሁሉ ሲደረግ ልብሱን ለባብሶ ሲነሳ እናትየው ግን ቆመው ነው። በዚህ አጋጣሚ ደረጇ ደብተሩን ይዞ አቤት ገብቶ ወንበሩ ላይ ይቀመጣል። ወንድምየውንም ትንሽ ቆም ብሎ በክፉ ዓይን ይመለከተዋል።

ሐናም ባዶ እጇን መጥታ እናቷ ስር ጠጋ ብላ እንደ ህፃን ሁሉ ወንድም ጣላ ሰካራሙ ስትል ትደመጣለች።

እናትዬውም ሐናን አንቺ ዘልዛላ ሂጂ ቡና ይፈላ ስኒውን አቀራርቢ ብለው ያዟታል። እንደ ታዘዘችው ለማድረግ ወደ ጓዳ ገባ ብላ ሲኒውን አመጣጥታ ስታጣጥብ ይታያል። ይሄ ሁሉ ሲሆን ማታ ነበር።

ደረጇም ይህን ጊዜ ሐናን ወደ ውጭ ጠርቶ የሆነ ነገር ላደርግ ስለሆነ አትደንግጪ ይላታል። እናትየውም ምንድን ነው የሚልሽ ሲሏት መጣሁ በሎ ሂደ ትልና ቁጭ ብላ ከናቷ ጋር ሆና ወንድም ጥላን ሲመክሩ ሲጫወቱ ቡና ሲጠጡ ጊዜው በጣም መሸ።

ወንድም ጥላ፡- ሰአት አየት አድርጎ እማዬ ከምሽቱ 4 ሰአት ሆነኮ ልጁስ የት ጠፋ። እራት የለም እንዴ? እሱ ሲመጣ ይብላ አቅርቡልን በልተን እንተኛ። በኔ ስካር ተበሳጭቶ ጠፍቶ እንዳይሆን ብቻ ብሎ ለሽንት ወጣ ይላል።

እናትዬውም፡- እውነትህን ነው ልጄ የትላንቱ ስካርህ የሚያስጠፋ ነው ይላሉ። ይላሉ ወጣ ሲል። እስኪመለስ ማዕድ ተዘጋጅቶ ይጠብቀዋል። ገብቶ ሲቀመጥ ሐና ታስታጥበዋለች።

ታጥበው ሲበሉም ወንድምዬው ደረጇ፡- እየተወለጋገደ አፉ ተሳስሮ እንደ ሰከረ ሰው አፉ ተሳስሮ ወደ ቤት ይገባል።

እናትዬውም በድንጋጤ ተነስተው፡- ወይኔ ልጄን አይኔ በጠፋ አንድአለኸኝ የምልህ ምን ነካህ ልጄ። አሁንስ እንዲያው በሞትኩ ይላሉ።

ሐናም፡- ወይኔ ደሬ ምን ነካህ?

ደረጇ፡- ምን ነካኝ አልኳችሁ ወንድም ጥላ ብች ነው የመጠጣት መብት ያለው? ቆይ ቆይ ቆይ ማነው ላንተ ብቻ መብቱን የሰጠህ? ብሎ ያፈጥበታል።

ወንድም ጥላም፡- የእውነት የሰከረ መስሎት እሺ ማንም መብት አልሰጠኝም ና እንጀራ እንብላና ትተኛለህ ብሎ ቢያባብለው እሱ ግን እየተቆጣ አሻፈረኝ ብሎ አስቸገረ። አንተ ነህ የምታበሳጭ? አንሺ አቦ ይሄን ትሪ እንዳልገለብጠው ይላል። ሲይዙትም አቦ ተውኛ ብሎ ያመነጫጭቃቸዋል።

ደረጇ፡- ሰካራም ቤት አይሰራም ሞት አይፈራም ይልና ቢፈልግ ይሰራል ባይፈልግ አይሰራም። አቦ ምንትገተራለህ እዚያ ቁጭ ብለህ ሆድህን ሙላ። እኔ ገና ሂጀ እጠግለሁ ይላል። እናትህን እንኳ አትፈራም ይሉታል።

ይህን ጊዜ ከዚህ ቤት ንቅንቅ አትላትም ብሎ ሲቆጣው

አንተም የዚህን ያህል ታናድደናለህ፣ ታስቸግረናለህ ፣ ታበሳጨናለህ። አየህ ወንድም ጥላ ስካር ምን ያህል እንደሚያስጠላ። እኔን መስታውት አድርገህ እራስክን እንድትመለከት ምሳሌ ለመሆን ነው እንጂ የሞተው አባቴ ይመለሳል ቢባል መጠጥ አልጠጣም። አንተ ግን ከዚህ በላይ ነው የምታስቸግረን።

ሐና፡- እማዬ የውነት መስሎሽ ደነገጥሽ አይደል። እኔም ሳስመስል ነው እንጂ ነግሮኝ ነው የወጣው።

እናት፡- በይ ተይኝ ልጄ እንዴት ከራማዬ ቦነነ መሰለሽ። ለሁሉም ሁለታችሁም ለኔ የሚበጅ ስራ አልሰራችሁም። አንተም ልጄ ተወው እስኪ ታናሽ ወንድምህ ይህን ያህል ተሳቆ ምሳሌ ሲያዘጋጅልህ ትንሽ አይሰማህም።

ወንድም ጥላ፡- በቃ በቃ ከዛሬ ጀምሮ በአባታችን አጥንት እና በእናቴ ከሁሉም በላይ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ገብቻለሁ ሁለተኛ አልጠጣም ሲል መጋረጃው ይዘጋል።

ተፈፀመ